# ፲ኛ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ለሙዓለ ህፃናት ወላጆች መመሪያ

በ፲ኛ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ፣ የሙዓለህፃናት ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጹት ላይ መመሪያ እና ጽንሰሃሳቦችን አግኝተዋል።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በግራጫማ ቀለም የሚታዩትን ክህሎቶች እና ጽንሰሐሳቦች ተምረዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ አልተመዘበም።

## የሂሳብ ትምህርት

### መቁጠርና መሰል ኣሃዞችን/ተራ ቁጥር መለየት

- ስንት እንደሆኑ ለማወቅ ነገሮችን መቁጠር።
- ቁጥሮችን በመጻፍ ብዛቶችን በኣንድ ቁጥር መወከል።
- ተመጣጣኝ (እኩል) ስብስቦችን መስራት።
- በታወቀ መደብ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሳይቆጥሩ (ሳይገምቱ) መለየት።
- ባለ-ኣስር-ማእቀፍ መዋቅር ብዛቶችን በተለመደ መደብ ውስጥ እንደ ሌላ መንገድ እንዲወክሉ መተግበር።
- እያንዳንዱ የተከታታይ ቁጥር ስም በቆጠሩ ቁጥር ኣንዱ እየጨመረ ለሚሄድ እንድ ብዛት እንደሚያመለክት ግንዛቤን መተግበር።

### መለካት እና ኣሃዞች/መረጃዎች

- እንደ ርዝመት ወይም ክብደትን የመሳሰሉ፣ ሊለኩ የሚችሉ ነገሮችን ባህሪያት ያብራሩ። የአንድን ነገር በርካታ ሊለኩ የሚችሉ ባህርያትን መግለጽ።
- ኣንድ ሊለካ የሚችል ባህርይ በጋራ ያላቸው ሁለት ነገሮችን በቀጥታ ማወዳደር፣ የትኛው ነገር ከባህሪው "የበዛ"/"ያነሰ" እንዳለው ለማየት፣ እናም ልዩነቱን መግለፅ። ለምሳሌ፣ የሁለት ልጆች ቁመታቸውን በቀጥታ በማወዳደር እና ኣንዱ ይበልጥ ረዥም/ያጠረ ብሎ መግለጽ።
- ቁሳቁሶችን ወደ ተለያዩ ምድቦች ይመድቧቸዉ፤ በእያንዳንዱ ምድብ ያሉትን ቁሳቁሶች በመቁጠር እያንዳንዱን ምድብ በቁጥሩ መጠን/ብዛት ለይ። (የፈርጅ ቆጠራን ከ10 ጋር እኩል ወይም ያነሱ እንዲሆኑ መወሰን)።

### ጂኦሜትሪ

- በኣካባቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን በቅርፆች ስም መግለፅ፣ እና የነዚህን ነገሮች ኣንፃራዊ ቦታዎች በላይ፣ በታች፣ በስተጎን፣ በፊት፣ በስተኋላ፣ እና ኣጠገብ የመሳሰሉ ቃላት በመጠቀም መግለፅ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- ያንድን መፅሃፍ የፊት ሽፋን፣ የኋላ ሽፋን፣ እና የርእስ ገፅን መለየት።
- በማስታወስ እና በመደገፍ የአንድን ታሪክ ገጸባህርይ ለይ።
- በማስታወስና በድጋፍ ቁልፍ ስለሆኑ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን ጠይቅ/ቂ።
- በዓላማ እና በመረዳት ከባድ ጽሑፍን በቡድን የማንበብ ተግባር ላይ በንቃት ተሳተፍ/ፊ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- ያንድን መፅሃፍ የፊትሽፋን፣ የኋላ ሽፋን፣ እና የርእስ ገፅ መለየት።
- በማስታወስና በድጋፍ በጽሑፍ ላይ ስለሚገኙ ቁልፍ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን መልስ/ሺ።
- በማስታወስ እና በድጋፍ በስዕል/በመግለጫ እና በጽሑፍ መካከል ያለውን ግንኙነት አስረዳ/ጂ።
- በዓላማ እና በመረዳት ከባድ ጽሑፍን በቡድን የማንበብ ተግባር ላይ በንቃት ተሳተፍ/ፊ።

### መሰረታዊ ክሂሎቶች

- ቃላቶችን ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከላይ ወደ ታች፣ እና ገጽ -በ-ገጽ ተከተል/ይ።
- የንግግር ቃላት የፊደላትን ቅደምተከተል በያዘ ቋንቋ በጽሑፍ እንደሚገለጹ ተገንዘብ/ቢ።
- በጽሑፍ ላይ ቃላት የሚለያዩት በመካከል ባለ የቦታ ርቀት መሆኑን ተረዳ/ጂ።
- የላይኞቹን እና የታችኞቹን ፊደላትን በመለየት ስሞችን ጥራ/ሪ።
- ቤት የሚመቱ ቃላትን ለይተህ(ሽ) ፍጠር/ሪ።

### ቋንቋ፡- የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም

- ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት ጮሆ ለተነበበ ፅሁፍ ግንዛቤ ማረጋገጥ።
- እርዳታ ለማግኘት፣ መረጃዎች ለማግኘት፣ ወይም ያልገባን ነገር ለማብራራት ጥያቄዎችን ማቅረብና መመለስ።

### ተጨማሪ የንባብ መረጃ

ተጨማሪ የምንባብ መረጃ ብቃት ያላቸው ኣንባቢዎች ለማበልፀግ ተፈላጊና ኣይነተኛ ስለሆኑ ክሂሎቶች መረጃዎች ያካትታል።

- ከፍተኛ የድግግሞሽ ቃላት (ከ44 ውስጥ)
- ፊደላትን መለየት ስማቸውን መጥራት-የላይኞቹ ፊደላት (ከ26 ውስጥ)
- ፊደላትን ለይቶ ስማቸውን መጥራት-የታችኞቹ ፊደላት (ከ26 ውስጥ)
- የመጀመርያዎቹ ኮንሶናንት ድምፆች (ከ19 ውስጥ)

## ጽሑፍ

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- ስለምታውቃቸው/ስለምታውቂያቸው ሰዎች፣ ቦታዎች፣ ወይም እቃዎች፣ ፍንጭ በመስጠት ከድጋፍ ጋር ግለጽ(ጪ)።
- በጋራ ቋንቋ እንቅስቃሴዎች ሙሉ ኣረፍተነገሮችን ማፍለቅ።
- ከኣዋቂዎች ኣመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፅሁፍን ለማጠናከር ከእኩያዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ሃሳቦች ምላሽ መስጠት።
- ተጨማሪ ዝርዝሮች ለማቅረብ ለገለፃዎች ስእሎች ወይም የሚታዩ ትርእይቶች መጨመር።

### የሃሳቦችና የኣስተያየቶች ኣገላለጽ

- ስለ አንድ ክውነት ወይም በርካታ የተያያዙ ክውነቶች እና ስለሆነው ነገር ግብረመልስ ላይ ትረካ ለማቅረብ ሥዕሎችን፣ ገለጻ፣ እና ጽሑፍ ተጠቀም/ሚ።
- ስለተለመዱ/የሚታወቁ ሰዎች፣ ቦታዎች ወይም ቁሳቁሶች ግለጽ/ጪ።
- ከተሞክሮዎች መረጃዎችን ማስታወስ።

የሃሳቦችና የኣስተያየቶች ኣገላለጽ

### የቋንቋ ኣጠቃቀም

- ሙሉ ኣረፍተነገሮችን መስራትና ማስፋፋት።
- ቀላል ቃላትን ፊደሎች በድምፅ መዘርዘር/Spell።
- ለኣብዛኞቹ ኮሶናንት ድምፆች ኣንድ ፊደል ወይም ፊደሎች መፃፍ።
- ኣዘውትረው የሚከሰቱ ስሞችንና ግሶችን ኣገልግሎት ላይ ማዋል (ለምሳሌ፣ ወንድ ልጅ፣ ውሻ፣ ልጃገረድ፣ መምህር፣ መማርያ ክፍል፣ ኣሳ፣ መሮጥ፣ ጡብ ጡብ ማለት፣ መጫወት፣ መፃፍ)።

## ሳይንስ

### መሬትና የህዋ ሳይንሶች

- የአየር ሁኔታዎች ባህርያትን መለየትና መግለፅ።
- አየሩን መታዘብና የአየሩን ሁኔታ ለመመዝገብ በስእሎች፣ ምስሎች፣ ወይም በቃላት መግለገል።
- በጊዜ ሂደት የአየር ሁኔታዎችን ለመለየት፣ ለመግለፅ፣ እና ለማነፃፀር የአየር ሁኔታ መረጃ መግለገል።
- የአየር ቅጦች/ሁኔታዎችን በየወቅቱ (ማለት፣ ፎል፣ ዊንተር፣ ስፐሪንግ እና ሰመር) መለየት።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ዜግነት

- በመማርያ ክፍል ዉስጥ ስለ መብቶች እና ግዴታዎች መለየትና መግለፅ።
- ስለ ት/ቤት እና የቤተሰብ አባላት (ለምሳሌ:- መምህር/ት፣ ተማሪ፣ ርእሰመምህር/ት፣ ልጅ/ህፃን፣ ወላጅ) ሚናቸውን እና ኃላፊነቶቻቸውን በመለየት አስረዳ/ጂ።
- ከዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ጋር የተያያዙ ምስሎች (ለምሳሌ፣ የአሜሪካ ሰንደቅ አላማ፣ ስታቱ ኦፍ ሊበርቲ) መለየትና መሰየም።
- የአሜሪካ መሪዎችንና ታሪካዊ ሰዎችን አስተዋፅኦ መለየትና መግለፅ።

## መረጃ/ኢንፎርሜሽን ማንበብ እና መጻፍ

- የግል መረጃ ፍላጎት መለየት።
- አንድን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ጥያቄዎችን መፍጠርና ማጣራት።
- መረጃን ለማግኘት በተለዩ ምንጮች መጠቀም።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብ መፍጠርና መገናኘት

- ከእይታ፣ ከትዉስታ፣ እና ከአይነህሊና ሃሳቦችን በሚታይ ለመወከል በቀለም፣ መሰመር፣ ቅርፅ፣ በአይነተ ሸካራነት፣ እና በፎርም መጠቀም።
- አስተሳሰብን ለመግለፅ የቀለም፣ መስመር፣ ቅርፅ፣ በአይነተ ሸካራነት፣ እና የፎርምን ጥቅሞች የሚዳስሱ የስነጥበብ ስራዎች መፍጠር።
- በስነጥበብ ስራዎች ቀለምን፣ መስመር፣ ቅርፅ፣ በአይነተ ሸካራነት፣ እና ፎርምን መለየትና ኣገግሎት ላይ ማዋል።

### ስነጥበብን ማቅረብና ምላሽ መስጠት

- በአካባቢ የሚገኙ ቀለሞች፣ መስመሮች፣ ቅርፆች፣ በአይነተ ሸካራነቶች፣ እና ፎርሞችን መግለፅ።
- ቀለምን፣ መስመር፣ ቅርፅ፣ በአይነተ ሸካራነት፣ ፎርምን፣ እና የንድፍ መሰረታዊ መርሆዎችን በስነጥበብ ስራዎች መለየት።
- ምርጥ የስነጥበብ ስራዎችን መታዘብ፣ መግለፅ፣ እና ምላሽ መስጠት።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- ድምፅን በተለያዩ መንገዶች (በንግግር፣ በሹክሹክታ፣ በመጣራት፣ በዝማሬ) በመለየት መጠቀም።
- ድምጾችን ፈጣን ወይም ዝግ ያለ በማለት መለየት እና በማይቆራረጥ ምት በተለያዩ ፍጥነቶች፣ አወራረዶች/ምቶች፣ መጫወት።
- በመንቀሳቀስ እና በመማርያ ክፍል መሳርያዎች በመጠቀም የማያቋርጥ ምት መጫወትና መዳሰስ።
- ድምፅን በተለያዩ መንገዶች የሚጠቀሙ ዘፈኖችን መዝፈን።
- የዝማሬ ጨዋታዎችን እና የጣት ጫወታ በማዳመጥ እየተጫወትክ(ሽ)፣ በደረሷቸው/በፈጠሯቸው ሰዎች ህይወት ላይ የነበራቸውን ጥቅም እና ፋይዳ አስረዳ(ጂ)።

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- ድምፅን በተለያዩ መንገዶች መጠቀምን ለይ:- ሹክሹክታ፣ በመጮኽ፣ በንግግር፣ እና በዝማሬ።
- በሙዚቃ ናሙናዎች ውስጥ ድምፆችን እንደ ፈጣን እና ዘገምተኛ ብሎ መለየት።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና ፅንሰሃሳቦች

- አስተማሪ ለሚ(ምት)ሰጠው የምልክት/ፍንጭ፣ በአንድ እግር መዝለል/hop፣ ዝላይ/jump፣ መጋለብ/gallop፣ እና ሸርተቴ/slide ምልክቱን መለየት ወይም መተግበር/ማሳየት።
- መታጠፍ/ማጎንበስ፣ መንጠራራት፣ መጠማዘዝ፣ እና መዞር በግል-ቦታ መለየት ወይም ማሳየት።
- ለማድረግ የሚያስፈልጉ ምልክቶችን/ፍንጮችን በመሥራት አሳይ ወይም ለይበአንድ እግር መዝለል/hop፣ ዝላይ/jump፣ መጋለብ/gallop፣ እና ሸርተቴ/slide ጥሩ በሆነ ቦታ ላይ በደህና በመጓዝ አሳይ።

### የግል እና የማህበራዊ ሃላፊነት

- በአካል ማጠንከርያ ትምህርት ውስጥ ኣገልግሎት ላይ የሚውሉ ህጎችና ልምዶችን መለየትና ማሳየት።
- አክብሮትን፣ ትብብርን፣ እና ኃላፊነትን ለይተህ/ሽ አሳይ እና በአካል ጥንካሬ ትምህርት የአክብሮትን፣ ትብብርን፣ እና ኃላፊነት አስፈላጊነት አስረዳ/ጂ።

## የጤና ትምህርት

### የአእምሮና የስሜት ጤንነት (MH)

- የመገናኛ መንገዶችን ማወቅ።
- ለተለያዩ ሁኔታዎች ስሜቶችን እና ምላሾችን ማገናዘብ።
- ስለ አንድ ሰው አዎንታዊ እና አሉታዊ ልዩ ገፀባሕርይ የሚዳርጉ ባህርያትን መለየት።

### አልኮል፣ትምባሆ/ሲጋራ፣ እና ሌሎች መዳኒቶች (ATOD)

- ተገቢ የመድኃኒት አጠቃቀሞችን ለይተህ እወቅ/ቂ።